


በፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን

# “አልጥልህም፥ አልተውህም”

***. . . የሰማይ አባታችን የሚያጋጥሙንን ፈተናዎች ስንቋቋምና ስንድናቸው በእነርሱም ለመማር፣ ለማደግና፣ ለመጠናከር እንደምንችል ያውቃል።***

በዚህ ምሽት በማስታወሻዬ ውስጥ እንዲህ ብዬ እጽፋለሁ፣ “ይህ ከተካፈልኳቸው አጠቃላይ ጉባኤዎች ውስጥ ሁሉ የሽኛው ከሁሉም በላይ የሚያነሳሳ ነው። ሁሉም ነገሮች ከሁሉም ታላቅ እና የመንፈሳዊ ጉዳዮች ነበሩ።”

ወንድሞችና እህቶች፣ ከስድስት ወር በፊት በዚህ አጠቃላይ ጉባኤ ስንገናኝ፣ ውድ ባለቤቴ ፍራንሲስ በአደገኛ ሁኔታ ወድቃ በሆስፒታል ተኝታ ነበር። በግንቦት ጉዳቷን ለማሸነፍ ከታገለች በኋላ፣ ወደ ዘለአለም ሄደች። የእርሷ ሞት ከባድ ነበር። እርሷ እና እኔ በጥቅምት 7 ቀን 1948 ዓ.ም በሶልት ሌክ ቤተመቅደስ ተጋብተን ነበር። ነገ የተጋባንበት 65 አመትን እናከብር ነበር። እርሷ የህይወቴ ፍቅር፣ የማምናት፣ እና ቅርብ ጓደኛዬ ነበረች። ትናፍቀኛለች ብዬ ብናገር የእኔን ስሜት የሚገልጽ አይደለም።

ይህ ጉባኤ በፕሬዘደንት ዴቪድ ኦ መኬይ እንደ አስራ ሁለት ሐዋርያ የተጠራሁበት 50 አመት ይማከብርበት ነው። በእነዚህ አመቶች በሙሉ የውድ ጓደኛዬን ሙሉ እና ፍጹም ድጋፍ ተሰምቶኛል ። ጥሪዬን እንዳከናውን ያደረገችው መስዋዕቶች መቆጠር አይቻሉም። ከእርሷ እና ከልጆቼ ለብዙ ቀናትና አንዳንዴም ሳምንታት በመራቅ በሀላፊነት የተሰጠኝን ሳከናውን በምንም የቅሬታ ቃል ከእርሷ ሰምቼ አላውቅም። በእርግጥም  መልዓክ ነበረች።

ፍራንሲስ ከሞተች በኋላ ለእኛ ለነበረው ምክር የእኔንና የቤተሰቤን ምስጋና ለማቅረብ እፈልጋለሁ። ብዙ መቶ ካርዶችና ደብዳቤዎች ለእርሷ ያላቸውን አድናቆት በመግለጽ እና ለቤተሰባችንም የሀዘን መግለጫን ተልከውልን ነበር። ብዙ ደርዘን የአበባ ቅንብሮችን ተቀብለናል። በእርሷ ስም ለቤተክርስቲያኗ አጠቃላይ የሚስዮን ገንዘብ በበጎ ድርጊት ለተሰጡትም እርዳታዎች አመስጋኝ ነን። ትታን በሄደችው ሰዎች ስምም፣ በልብ ከመጣውና ለደግ ቃላቶቻችሁም ታልቅ ምስጋና አቀርባለሁ።

በዚህ በመለያየታችን ጊዜ ለእኔ ከፍተኛ ምቾት ይሰጠኝ የነበረው ስለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ያለኝ ምስክርነት እና ውዷ ፍራንሲስ ህያው እንደሆነች በማወቄ ነው። መለያየታችን ጊዜአዊ እንደሆነ አውቃለሁ። በምድር እና በሰማይ ውስጥ ለማስተሳሰር ስልጣን በነበረው ሰው በእግዚአብሔር ቤት እንደተሳሰርን አውቃለሁ። አንድ ቀን እንደገና እንደምንገናኝ እና በፍጹም እንደገና እንደማንለያይ አውቃለሁ። ይህም እውቀት ይደግፈኛል።

ወንድሞችና እህቶች፣ ማንም ሰው ሀዘን እና ስቃይ ሳያገኝ አይኖርም ለማለት አይቻልም፣ ወም በሰው ዘር ታሪክ ውስጥ መተራመስና መሰቃየት ያልነበረበት ጊዜ የለም።

የህይወት መንገድ ወደ መጥፎ ሁኔታ ሲዞር፣ “ለምን እኔን?” የሚል ጥያቄ ለመጠየቅ መገፋፋት ይኖራል። አንዳንዴ ችግሩ መጨረሻ የሌለው ይመስላል፣ ጨለማውን የሚያጠፉ የጸሀይ ብርሀን ያለም አይመስልም። በተሰበረ አላማ ተስፋ በቆረጥ እና በጠፉ ተስፋዎች ፍርሀት ምክንያት እንደተከበብን ይሰማንል። በመፅሐፍ ቅዱስ ያለምንም ልመና እንዲህ እንደግማለን፣ “በገለዓድ የሚቀባ መድኃኒት የለምን?”[1] እንደተረሳን፣ ልባችን እንደተሰበረ፣ እና ብቸኛ እንደሆንን ይሰማናል። የግል መጥፎ እድላችንን መጥፎ ሀሳብ ባለበት አስተያየት እንመለከተዋለን። በአብዛኛው ጊዜ የሰማይ ትዕግስት እንደሚያስፈልግ እየረሳን፣ ለችግራችን መፍትሄ ለማግኘት እንቸኩላለን።

የሚመጡብን ችግሮች ለመፅናት ያለንን ችሎታ ይፈትኑልናል። በእያንዳንዳችን መመለስ ያለ መሰረታዊ ጥያቄም አለ፥ ልደናቀፍ፣ ወይስ ልፈፅም? አንዳንዶች ከፈተናቸው በላይ ከፍ ለማለት በማይችሉበት ምክንያት ይደናቀፋሉ። አንዳንዶች ፈተናቸውን ለመቋቋም ባለመቻላቸው እየተደናቀፉ ይገኛሉ። ለመፈጸም እስከ ህይወት መጨረሻ ድረስ መፅናትን ያስፈልገዋል።

የሚደርሱብንን ነገሮች ስናስብባቸው፣ ከጥንቱ ኢዮብ ጋር “ሰው እንዲሁ ለመከራ ተወልዶአል” እንላለን።[2] ኢዮብ “ፍጹምና ቅን፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፉትም የራቀ”3 ሰው ነበር።[3] በሚያደርገው ጻድቅ፣ በንብረቱ ሀብታም የነበረው ኢዮብ ማንንም ሰው ሊያጠፋ ይችል የነበረ ፈተና አጋጠመው። ንብረቶቹን አጥቶ፣ በጓደኞቹ ተሰድቦ፣ ተሰቃይቶ፣ ቤተሰቡን በማጣት አዝኖ፣ “እግዚአብሔርን ስደብናሙት”4 ተብሎ ነበር።[4] ይህን ፈተና ተቋቋመ እናም ከልዑል ልቡም እንዲህ በማለት አወጀ፥

“አሁንም፥ እነሆ፥ ምስክሬ በሰማይ አለ፥ የሚመሰክርልኝም በአርያም ነው።”[5]

የሚቤዠኝ ሕያው እንደ ሆነ አውቃለሁ።[6]

ኢዮብ እምነቱን ቀጠለ። ወደ እኛ የሚመጡት ፈተናዎች ሲያጋጥሙን እንደ ኢዮብ እናደርጋለን?

በህይወት ምታት ምክንያት ሸከም እንዳለን ሲሰማን፣ ሌሎች እንዲህ አጋጣሚ እንደነበራቸው፣ እናም እንዳሸነፉት እናስታውስ።

በዚህ የጊዜዎች ፍጻሜ ዘመን ውስጥ የቤተክርስቲስያኗ ታሪክ ትግል ቢኖርባቸውም ቀጥተኛና ደስተኛ በሆኑት አጋጣሚዎች የተሞላ ነው። ምክንያቱ ምንድን ነው? የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን የህይወታቸው ዋና ክፍል አድርገውታል። ከሚያጋጥመን የሚያድነንም ይህ ነው። አስቸጋሪ ፈተናዎች ይኖሩናል፣ ነገር ግን እነዚህን ለመቋቋ እና ለማሸነፍ ችሎታ ይኖረናል።

ከበሽታ መኻታ፣ በእምባ ከረጠበ ትራስ፣ “አልጥልህም፥ አልተውህም”7 በሚለው በመለኮታዊ ማረጋገጫ እና ውድ ቃል ኪዳን በሰማይ ከፍ እንላለን። እንደዚህ አይነት መፅናኛ ታላቅ ዋጋ አለው።[7] እንደዚህ አይነት መፅናኛ ታላቅ ዋጋ ያለው ነው።

በአለም አቀፍ የጥሪዬን ሀላፊነት ለማሟላት እሩቅ እና በስፋት ስጓዝ፣ ብዙ ነገሮችን ለማወቅ ችያለሁ — ከእነዚህም ታናሽ ያልሆነውም ሀዘን እና ስቃይ ሀለንተናዊ እንደሆነ ነው። በሀዘን ያሉትን፣ የታመሙትን፣ ከጋብቻ መፋታት የሚያጋጥማቸውን፣ መንገዳቸውን ያጡ ልጆች ያላቸውን፣ ወይም በኃጢያት ምክንያት የሚሰቃዩትን ስጎበኝ ለመግለጽ የማይቻል የልብ መሰበር እና ሀዘን ተመልክቻለሁ።

ዝርዝሩ ረጅም ነው፣ ምክንያቱም ሊደርሱብን የሚችሉ ችግሮች ለመቆጠር አይቻሉምና። አንድ ምሳሌን አውጥቶ ለመጠቆም አስቸጋሪ ነው፣ ግን ስለፈተና ሳስብ ሀሳቤ በልጅነቴ የሰንበት ትምህርት አስተማሪ ስለነበሩት ወንድም ብረምስ ይሄዳል። እርሳቸውም ወርቃማ ልብ ያላቸው ታማኝ የቤተክርስቲያኗ አባል ነበሩ። እርሳቸው እና ባለቤታቸው ሴዲ ስምንት ልጆች ነበሯቸው፣ እድሜአቸውም ከእኛ ቤተሰብ ካሉት ጋር አንድ የሆነ ነበር።

ፍራንሲስ እና እኔ ከተጋባንና ከዎርዱ ከወጣን በኋላ፣ ወንድም እና እህት በርምስ እና ቤተሰቢቻቸውን በጋብቻና በለቅሶዎች ጊዜ እናያቸው ነበር።

በ1968 ዓ.ም (እ.አ.አ) ወንድም በርምስ ባለቤታቸውን ሴዲን በሞት አጡ። አመቶችም ሲያልፉ ከስምንቱ ሁለት ልጆቻቸውም ሞቱባቸው።

ከ13 አመት በኋላ አንድ ቀን፣ የወንድም ብረም የልጅ ልጅ በስልክ ደወለችልኝ። አያቷ 105ኛ አመታቸው ላይ እንደደረሱ አብራራች። እንዲህም አለች፣ “በትንሽ መንከባከቢያ ቦታ ይኖራሉ፣ ግን በየሳምንቱ በሰንበት ከቤተሰባቸው ጋር ተገናኝነትው የወንጌል ትምህርትን ያስተምራሉ።” ቀጥላም፣ “ባለፈው እሁድ አያታችን እንዲህ አሉን፣ ‘ውዶቼ፣ በዚህ ሳምንት እሞታለሁ። ቶሚ ሞንሰንን እባካችሁ ጥሩልኝ። ምን መደረግ እንደሚገባ ያውቀዋል።’ ”

ወንድም ብረምስን በሚቀጥለው ምሽት ጎበኘኋቸው። ለብዙ ጊዜ አይቻቸው አላውቅም ነበር። መስማት ስለማይችሉ ላነጋግራቸው አልቻልኩም። አይናቸው ስለማያይ እንዲያነቧቸው የሚችሉትን መልእክት ልፅፍላቸው አልቻልኩም። ቤተሰባቸው ሊያነጋገሯቸው የሚችሉት የቀኝ እጃቸውን ይዘው የሚጎበኘውን ሰው ስም በግራ እጃቸው ላይ በመጻፍ እንደሆነ ተነገረኝ። ምንም መልእክቶች በዚህ ዘዴ ይሰጧቸው ነበር። የነሩኝን ተከትዬ በእጃቸው ላይ በልጅነት በሚያውቁኝ ስም “ቶሚ ሞንሰን” በማለት ጻፍኩኝ። ወንድም ብረምስ ተደሰቱ፣ እናም እጆቼን ወስደው በራሳቸው ላይ አሳረፉ። ፍላጎታቸው የክህነት በረከት ለመቀበል እንደሆነ አወቅሁኝ። ወደ መንከባከቢያው ቦታ የወሰደኝ ሾፌር ከእኔ ጋር ሆኖ እጆቻችንን በወንድም ብረምስ ራሳ ላይ ጫንን እና የተፈለገውን የክህነት በረከት ሰጠን። ከዚያም በኋላ እምባ ብርሀን ከሌላቸው አይኖቻቸው ፈሰሰ። እጆቼንም በምስጋና አጥብቀው ያዙ። ምን እንኳን የሰጠናቸውን በረከት ለመስማት ባይችሉም፣ መንፈስ በዚያ ጠንካራ ነበር፣ እናም ያስፈለጋቸውን በረከት እንደሰጠናቸው ለማወቅ መነሳሻ እንደነበራቸው አምናለሁ። ይህ አስደሳች ሰው ለማየት አይችሉም ነበር። ለመስማትም አይችሉም ነበር። በሚንከባከቡበት ቦታ በቀንም ይሁን በምሽት በትንሽ ክፍል ውስጥ ይቀመጡ ነበር። ነገር ግን በፊታቸው የነበረው ፈገግታ እና የተናገሩት ቃላት ልቤን ነክተው ነበር። “አመሰግናለሁ፣”አሉ። “የሰማይ አባቴ ለእኔ በጣም መልካም ነበር።”

ከሳምንት ውስጥ፣ ልክ ወንድም ብረምስ እንዳሉት ሞቱ። ባልነበራቸው ላይ አላተኮሩም፤ ግን ለነበራቸው ብዙ ለነበራቸው በረከቶች ዝልቅ ምስጋና ሁልጊዜም ነበራቸው።

የሚያስደስቱን ብዙ ነገሮች የሚሰጠን የሰማይ አባታችን መቋቋም ባለብን ፈተናዎች ለመማር፣ ለማደግና፣ ለመጠናከር እንደምንችል ያውቃል። ልባችን የሚሰበርበት እና የምናዝንበት፣ የናለቅስበት፣ እና ምን ያህል እንደምንችል የሚመዝንበት ጊዜም እንደሚኖር ያውቃል። ነገር ግን፣ እንደዚህ አይነት ችግሮች ለሚሻል ሁኔታ እንድንቀየር፣ የሰማይ አባታችን በሚያስተምረን መሰረት ህይወታችንን እንድንገነባ፣ ከነበርንበት የተለየ፣ እንዲሁም የተሻለ እንድንሆን፣ ከዚህ በፊት የተሻለ እውቀት እንዲኖረን፣ የሌሎች ጉዳን የሚሰማን እንድንሆን፣ እና ከነበረን በላይ የሆነ ምስክሮች እንዲኖረን ያደርጉናል።

ይህም አላማችን መሆን ይገባዋል— በጸሀይ ብርሀን እና በጥላ ስንሄድም የምንቋቋምና የምንጸና፣ አዎን፣ ደግሞም በተጨማሪ በመንፈስ የተጣራን መሆን ይገባናል። በምናሸንፋቸው ፈተናዎች እና በምንቋቋማቸው ችግሮች ባይሆን ኖሮ፣ እንዳለንበት የዘለአለም ህይወት ወደሆነው አላማችን በትንሽም ይሁን በምንም አናድግም ነበር። ገጣሚው በሚቀጥሉት ቃላት ይህንንም ሀሳብ አቅርቦ ነበር፥

*ጥሩ እንጨት በቀላሉ አያድግም፣*
*ጠንካራው ንፋስ፣ ዛፉን ያጠናክራልና።*
*ሰማይም ሲርቅ፣ ርዝመቱ ታላቅ ነው፣*
*አውሎ ንፋሱ ሲጨምር፣ ጥንካሪውም ብዙ ነው።*
*በጸሀይና በብርድ፣ በዝናብና በበረዶ፣*
*በዛፍና ሰዎች፣ ጥሩ እንጨት ያድጋል።*[8]

መምህር ብቻ የፈተናችንን ዝልቅነት፣ ህመማችንን፣ እና የምንሰቃይበትን የሚያውቅው። በፈተና ጊዜ ዘለአለማዊ ሰላም የሚያቀርብልን እርሱ ብቻ ነው። የሚሰቃየውን ነፍሳችንን በሚያፅናኑ ቃላት የሚነካውም እርሱ ብቻ ነው፥

“እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።

“ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ”

“ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና።”[9]

መልካም ጊዜ ይሁን መጥፎ፣ እርሱ ከእኛ ጋር ነው። እንደማይቀየርም ቃል ገብቶልናል።

ወንድሞቼና እህቶቼ፣ በህይወት ፈተና ጊዜ የማይቀንስ እና የማይጨምር ለሰማይ አባታችን ታማኝነት ይኑረን። እርሱን ለማስታወስ ችግሮች እንዲያጋጥሙን አያስፈልጉን፣ እናም ለእርሱ እምነታችንን ለመስጠት ወደ ትሁትነት መገፋት አያስፈልገን።

ወደ ሰማይ አባታችን ለመቅረብ ሁልጊዜም እንጣር። ይህን ለማድረግ፣ ወደ እርሱ እንጸልይ እና በየቀኑም እርሱን እናድምጥ። የጸሀይ ብርሀን ወይም የዝናብ ቀን ቢሆኑም፣ በየሰአቱ በእውነት እርሱን እንፈልጋለን። እንዲህ የሚለው የእርሱ ቃል ኪዳን እኛ የምንፈልገው ይሁን፣ “አልጥልህም፥ አልተውህም።”[10]

በነፍሴ ጥንካሬ በሙሉ እግዚአብሔር ህያው እንደሆነ እንደሚያፈቅረን፣ አንድያ ልጁ ህያው እንደሆነ እና ለእኛ እንደሞተ፣ እናም የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በህይወታችን ጭለማ ሰብሮ የሚገባው ብርሀን እንደሆነ እመሰክራለጉ። ይህም እንዲሆን የምጸልየው በቅዱሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ አሜን።

ማስታወሻዎች
1.1. ኤርምያስ 8፥22
2.2. ኢዮብ 5፥7
3. ኢዮብ 1፥1
4. ኢዮብ 2፥9
5. ኢዮብ 16፥19
6. ኢዮብ 19፥25
7. ኢያሱ 1፥5
8. Douglas Malloch, "Good Timber," quoted in Sterling W. Sill, *Making the Most of Yourself* 1971), 23።
9. ማቴዎስ 11፥28–30
10. ኢያሱ 1፥5

# ለጊዜአችን ትምህርቶች

የመልከጸዴቅ ክህነትና የሴቶች መረዳጃ ማህበር የአራተኛው እሁዶች ትምህርቶች "ለጊዜአችን ትምህርቶች" የተወከሉ ይሆናሉ። እያንዳንድ ትምህርትም በቅርብ ከነበረው የአጠቃላይ ጉባኤ አንድ ወይም ተጨማሪ ንግግሮች መምረጥ ይቻላል። የካስማ እና የአውራጃ መሪዎች የትኛዎቹ ንግግሮች መጠቀም እንደሚገባቸው መምረጥ ይችላሉ፣ ወይም ይህን ሀላፊነት ለኤጲስ ቆጶስ እና ለቅርንጫፍ መሪ ለመስጠት ይችላሉ። የመልከጼደቅ የክህነት ስልጣን ወንድሞች እና የሴቶች መረዳጃ ማህበር እህቶች አንድ አይነት ንግግሮችን በአንድ እሁድ ቀን ማጥናታቸው አስፈላጊነትን መሪዎች ደጋግመው ማሳሰብ ይገባቸዋል።

በአራተኛው ሰንበት ትምህርት ተሳታፊዎች የቅርቡን የአጠቃላይ ጉባኤ መጽሄት እንዲያጠኑ እና ወደ ክፍል እንዲያመጡ ይበረታቱ።

**ከንግግሮች ትምህርትን የማዘጋጃ ሀሳቦች**

ንግግሮችን ስታጠኑ እና ስታስተምሩ መንፈስ ቅዱስ ከእናንተ ጋር እንዲሆን ጸልዩ። ሌሎች መፅሀፎችን በመጠቀም ትምህርትን ለማዘጋጀት ሀሳብ ይመጣላችሁ ይሆናል፣ ነገር ግን የጉባኤ ንግግሮች የትምህርት መረጃ እንዲሆን ፈቃድ የተሰጠበት ነው። የተመደባችሁትም በቤተክርስትያኗ የቅርብ አጠቃላይ ጉባኤ ውስጥ የተሰጡትን ትምህርቶች ሌሎችን ወንጌሉን ለመኖር እና ለመማር እንድትረዱአቸው ነው።

የክፍል አባሎች ፍላጎትን የሚያሟሉ መሰረታዊ መርሆችን እና ትምህርቶችን በመፈለግ ንግግሮችን አጥኑ። ደግሞም ታሪኮችን፣ ቅዱስ መጻህፍት የተጠቀሱበትን፣ እና እነዚህን እውነቶች ለማስተማር የሚረዷችሁን ቃላቶች ፈልጉ።


መሰረታዊ መርሆችን እና ትምህርቶችን እንዴት እንደምታስተምሩም ዘርዝራችሁ ጻፉ። የክፍል አባላትን የሚረዱ ጥያቄዎችን አስቡባቸው።

- በንግግሮች ውስጥ መሰረታዊ መርሆችን እና ትምህርቶችን ፈልጉ።
- ስለትርጉማቸው አስቡበት።
- መረዳትን፣ ሀሳባቸውን፣ አጋጣሚያቸውን፣ እና ምስክሮችን አካፈሉ።
- እነዚህን መሰረታዊ መርሆች እና ትምህርቶች በህይወታቸው ይጠቀሙባቸው።

| ትምህርቶቹ የሚማሩበት ወራት | የአራተኛው እሁድ የትምህርት መርጃዎች |
|---|---|
| ጥቅምት 2013 (እ.አ.አ)–ሚያዝያ 2014 (እ.አ.አ) | በጥቅምት 2013 (እ.አ.አ) አጠቃላይ ጉባኤ የተሰጠ ንግግር* |
| ሚያዝያ 2014 (እ.አ.አ)–ጥቅምት 2014 (እ.አ.አ) | በሚያዝያ 2014 (እ.አ.አ) አጠቃላይ ጉባኤ የተሰጠ ንግግር* |

** ለሚያዝያ እና ለጥቅምት የአራተኛ ሰንበት ትምህርቶች፣ ወደፊት ከነበሩት ወይም በቅርብ ከነበሩት የጉባኤ ንግግሮች መምረጥ ይቻላል። እነዚህ ንግግሮች (በብዙ ቋንቋዎች) በ conference.lds.org ውስጥ ይገኛሉ።*

© 2013 by Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/13 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/13 (እ.አ.አ)
*First Presidency Message, November 2013*. Amharic. 10671 506 ትርጉም



**በፕሬዘደንት ዲየትር ኤፍ ኡክዶርፍ**
*የቀዳሚ አመራር ሁለተኛ አማካሪ*

# ኑ ከእኛ ጋር አንድ ሁኑ

***ጉዳዮቻችሁ፣ የግል ታሪኮቻችሁ፣ ወይም የምስክራችሁ ጥንካሬ ምንም ቢሆኑም፣ በቤተክርስቲያኗ ለእናንተ ክፍል አላችሁ።***

አንድ ጊዜ የአለም ሀይማኖቶች በተሰበሰቡበት አዳራሽ ውስጥ እንደሚገኝ ህልም የነበረው አንድ ሰው ነበር። እያንዳንዱ ሀይማኖት ተፈላጊና ብቁ የሆኑ ብዙ ነገሮች እንዳሉት መሰለው።

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን የሚወክሉ ሰዎችን አገኘና እንዲህ ሲል ጠየቀ፣ “እናንተ ከአባላቶቻችሁ ምን ትጠይቃላችሁ?”

“እኛ ምንም አንጠይቅም፣” ብለው መለሱ። “ነገር ግን ጌታ ሁሉንም እንድንቀድስ ይጠይቀናል።”

ሰዎቹም ስለቤተክርስቲያኗ ጢ፣ ስለ ቤት ለቤት ጉብኝት እና ስለሴቶች የቤት ለቤት ጉብኝት፣ ስለሙሉ ጊዜ ሚሲዮን፣ ስለየሳምንት የቤተሰብ የቤት ምሽት፣ ስለቤተመቅደስ ስራ፣ ስለ በጎ ድርገት አገልግሎቶች፣ እና ለማስተማር ስለሚመደቡበት ገለጹለት።

“ለሚሰሩት ስራዎች ሁሉ ሰዎቻችሁን ትከፍሏቸዋላችሁን?” ብሎ ሰውየው ጠየቀ።

“አይደለም፣” ሰዎቹ ገለጹ። “ጊዜአቸውን በነጻ ነው የሚሰጡት።”

ሰዎቹም ቀጥለው፣ “ደግሞም በየስድስት ወርም የቤተክርስቲያን አባላቶቻችን ወደ አጠቃላይ ጉባኤ ስብሰባ ለአስር ሰዓት ለመሳተፍ ይሄዳሉ ወይም ያዳምጣሉ።”

“ለአስር ሰዓት ሰዎች የሚናገሩበት?” በማለት ሰውየው ተደነቀ።

“የየሳምንቱስ የቤተክርስቲያን አገልግሎቶችስ? ምን ያህል ረጅም ናቸው?”

‘በእያንዳንዱ እሁድ ለሶስት ሰዓት!”

“ሰውየውም “ወየው” አለ። የቤተክርስቲያን አባላቶቻችሁ እንዳላችሁት በእርግጥ ያደርጋሉን?”

“ያንንም እና ተጨማሪም። “የቤተሰብ ታሪክን፣ የወጣቶች ሰፈራን፣ የሀይማኖት ስብሰባዎችን፣ የቅዱስ መጻህፍት ጥናትን፣ የአመራር ስልጠና፣ የወጣቶች መሳተፊያዎችን፣ የጠዋት ሰምነሪን፣ ቤተክርስቲያኗን መንከባከብን ገና አልጠቀስንም፣ እናም የጌታ የጤንነት ህግጋት፣ ድሆችን ለመርዳት በየወሩ የሚጾምበት፣ እና አስራትም አለ።”

ከዚያም ሰውየም አለ፣ “አሁን ግራ ተጋባሁ። ማንም ሰው ለምን የእንደዚህ አይነት የቤተክርስቲያናችሁ አባል ለመሆን ይፈልጋል?”

ሰዎቹም ፈገግ አሉና፣”ይህን የማትጠይቅ መስሎን ነበር” አሉት።

**ማንኛውም ሰው ለምን የእንደዚህ አይነት ቤተክርስቲያን አባል ይሆናል?**

በአለም አቀፍ የሚገኙ ቤተክርስቲያኖች በቁጥር እየቀነሱ በሚገኙበት ጊዜ፣ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ ከብዙዎቹ በቁጥር ትንሽ ብትሆንም፣ በአለም ከሚገኙ ቤተክርስቲያኖች በፍጥነት የምታድግ ናት። በመስከረም 2013 (እ.አ.አ) ጀምሮ ቤተክርስቲያኗ በአለም ውስጥ 15 ሚልዮን አባላት አላት።

ለዚህ ብዙ ምክንያቶች አሉ፣ ነገር ግን አንዳንዶችን ላቀርብ እችላለሁን?

*የአዳኝ ቤተክርስቲያን*

*መጀመሪያ*፣ ቤተክርስቲያኗ በዚህ በዘመናችን በዳግም የተመለሰችው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በዚህም በስሙ የመስራት ፣ እንዲሁም ለኃጢያት ስርየት ለመጥመቅ፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለመስጠት፣ እና በምድር እና በሰማይ ለማተም፣ ስልጣንን ታገኛላችሁ።[1]

የዚህ ቤተክርስቲያን አባል የሚሆኑ አዳኝ ኢየሱስ ክርስቶስን ያፈቅራሉ እናም እርሱን ለመከተል ይፈልጋሉ። እግዚአብሔር ለሰው ዘር እንደገና እንደሚናገር ባላቸው እውቀትም ይደሰታሉ። የቅዱስ ክህነት ሹመትን ሲቀበሉ እና ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ሲገቡ፣ በህይወታቸው የእርሱ ሀይል ይሰማቸዋል።[2] ወደ ቅዱስ ቤተመቅደስ ሲገቡ፣ በእርሱ ፊት እንደሚገኙ ይሰማቸዋል። ቅዱሳት መጻህፍትን ሲያነቡ[3] እናም በእርሱ ነቢያት ትምህርት ሲኖሩም፣ በጣም ከሚያፈቅሩት አዳኛቸው ጋር ቅርብ ይሆናሉ።

*ንቁ እምነት*

ሌላው ምክንያትም ቤተክርስቲያኗ መልካም ለማድረግ እድል መስጠቷ ነው።

በእግዚአብሔር ማመን ሙገሳ የሚያስፈልገው ነው፣ ነገር ግን አብዛኛው ሰዎች ከሚያነሳሳ ስብከቶች ወይም ከበላይ ከሚገኙት ቤቶች ለማዳመጥ በላይ ነው የሚፈልጉት።[4] እምነታቸውን ወደስራ ለመለወጥ ይፈልጋሉ። እጅጌአቸውን ጠቅልለው በታላቅ ስራ ለመሳተፍ ይፈልጋሉ።

ከእኛ ጋር አንድ ሲሆኑ የሚደርሰውም ይህ ነው— ችሎታዎቻቸውን፣ ርህራሄአቸውን፣ እና ጊዜአቸውን ወደ መልካም ስራ ለመቀየር ብዙ እድሎች ይኖሯቸዋል። በአለም አቀፍ ጉባኤዎቻችን ውስጥ የሚከፈላቸው መሪዎች ስለሌሉን፣ የአገልግሎት ስራዎችን አባላቶቻችን ያከናውኑታል። በመነሳሳት የተጠሩ ናቸው። አንዳንዴ በገዛ ፈቃደኞች ነን፤ አንዳንዴም ለእኛ ፈቃደኛነታችንን ሌሎች

ይናገሩልናል ሀላፊነቶችን እንደ ሸክም ሳይሆን እግዚአብሄርን እና ልጆቹን ለማገልገል በደስታ የገባናቸውን ቃል ኪዳኖች እንደምናሟላበት እድሎች እናያቸዋለን።

*እንደ ሀብት የምንመለከታቸው በረከቶች*

ሰዎች የቤተክርስቲያኗ አባላት የሚሆኑበት ሶስተኛው ምክንያትም የደቀመዛሙርት መንገድን መከተል ውድ ወደሆኑ በረከቶች ስለሚመሩ ነው።

ጥምቀትን በደቀ መዛሙርትነት ጉዞአችን እንደመጀመሪያ ቦታ እንመለከታለን። ከኢየሱስ ክርስቶስጋር በየቀኑ የምንራመደው በዚህ ህይወት ወደ ሰላም እና አላማ እናም በሚመጣው አለምም ወደ ታላቅ ደስታና ዘለአለማዊ ደህንነት ይመራል።

ይህን መንገድ በታማኝነት የሚከተሉ ብዙ ጉድጓዶችን፣ ሀዘኖችን፣ እና በህይወት ጸጸቶችን ያስወግዳሉ።

በመንፈስ ደህ እና በልብ ታማኝ የሆነ በዚህ ታላቅ የእውቀት ሀብቶችን ያገኛሉ።

የሚሰቃዩ ወይም የሚያዝኑም መፈወሻን በዚህ ያገኛሉ።

በኃጢያት ሸከም ያላቻውም ምህረትን፣ ነጻነትን፣ እና እረፍትን ያገኛሉ።

## ከተሳታፊነት ለሚርቁ

የእውነት ፍለጋ ብዙ ሚልዮን የሚሆኑ ሰዎችን ወደኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶች ቤተክርስቲያን መርቷቸዋል። ነገር ግን፣ አንድ ጊዜ ያፈቅሯት የነበረችውን ቤተክርስቲያን ትተው የሚሄዱ አንዳንዶች አሉ።

አንድም እንዲህ ይጠይቃል፣ “ወንጌል እንደዚህ አስደናቂ ከሆነ፣ ለምንድን ነው  ሰው ይህን ትተውት የሚሄዱት?”

አንዳንዴ እነርሱ ተከፍተዋል ወይም ሰነፍ ወይም ኃጢያተኛ በመሆናቸው ነው ብለን እናስባለን። በእርግጥ ይህ እንዲህ ቀላል አይደለም። በእርግጥም ለተለያዩ ጉዳዮች ለመጠቀም የሚቻል አንድ ምክንያት የለም።

አንዳንድ አባላት እራሳቸውን ከቤተክርስቲያኗ ለመለየት እንደሚገባቸው ባላቸው ጥያቄ ለብዙ አመታት ይታገላሉ።

ጥያቄንበጠየቀ እና መልስን በፈለገ ወጣት ሰው በዳግም የተመለሰችው የግል ነጻ ምጫን በጣም በምታከብር በዚህች ቤተክርስቲያን ውስጥ በታማኝነት እውነትን የሚፈልጉትን እናከብራለን። ከምናፈቅራት ቤተክርስቲያን እና ካገኘነው እውነት ወጥተው ሲሄዱ ልባችን ይሰበራል፣ ነገር ግን ሁሉን ቻይ እግዚአብሔርን፣ ልክ እኛ መመብት በምናደርገው፣ በህሊናቸው ውሳኔ መሰረት ለማምለክ ያላቸውን መብት እናከብራለን።[5]

## ያልተመለሱ ጥያቄዎች

አንዳንዶች ከዚህ በፊት በተባሉት ወይም በተደረጉት ላይ ባላቸው ያልተመለሱ ጥያቄዎች ይታገላሉ። በቤተክርስቲያኗ ታሪክ 200 አመታት ውስጥ ካልተቋረጠ ከተነሳሱ፣ ከተከበሩ፣ እና መለኮታዊ ከሆኑ ድርጊቶች ጋር ሰዎች ጥያቄ እንዲኖራቸው የሚያደርጉ የተባሉ እና የተደረጉ ነገሮች እንዳሉ በግልጽ እንቀበላለን።

አንዳንዴ መረጃዎች በሙሉ ስለሌሉን እና ትንሽ ትዕግስት ስለሚያስፈልገን ጥያቄዎች ይነሳሉ። ሁሉም እውነት በመጨረሻ ሲታወቅ፣ ከዚህ በፊት የማይገቡን ነግሮች በሚያረካን መንገድ መፍትሄ ያገኛሉ።

አንዳንዴ “ተጨባጭ ነገር” ምን እንደሆነ ያለ የተለያየ አስተሳሰብ ይገኛል። በአንዳንዶች ጥርጣሪን የሚያመጣው ጥያቄ፣ በጥንቃቄ ከተመረመረ በኋላ በሌሎች እምነትን ይገነባል።

## ፍጹም ያልሆኑ ሰዎች ስህተቶች

በግልጽ ለመናገር፣ አባላት ወይም የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ስህተት ያደረጉበት ጊዜ አለ። ከመሰረታዊ መርሆቻችን፣ ከመሰረቶቻችን፣ ወይም ከትምህርታችን ጋር የማይስማሙ ነገሮች ተብለው ወይም ተደርገው ይሆናል።የተባሉ ወይም የተደረጉ

ቤተክርስቲያኗ ፍጹም የምትሆነው ፍጹም በሆኑ ሰዎች ከተመራች ነው። እግዚአብሔር ፍጹም ነው፣ ትምህርቶቹም ንጹህ ነው። ነገር ግን —የእርሱ ፍጹም ባልንነው ልጆቹ — በኩል ይሰራል እናም ፍጹም ያልሆኑ ሰዎች ስህተት ይሰራሉ።

በመፅሐፈ ሞርሞን መግቢያ ገጽ ላይ ይህን እናነባለን፣ “እስከማሳመን—እና አሁን፣ ስህተቶች ካሉ ስህተቶቹ የሰዎች ስህተቶች ናቸው፣ ስለዚህ፣ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ያለ እንከን ትሆኑ ዘንድ የእግዚአብሔር የሆኑትን አትኮንኑ።”[6]

ይህም ሁልጊዜ እንደነበረበት ነው እናም ክርስቶስ በምድር ላይ ለመነገስ እራሱ እስከሚመጣበት ፍጹም ጊዜ ድረስ እንዲህም ይሆናል።

በሚያሳዝን ሁኔታ ግን አንዳንዶች በሰዎች በተሰሩ ስህተቶች ምክንያት ተደናቅፈዋል። ነገር ግን ይህ ቢሆንም፣ በኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኘው ዳግም የተመለሰው ዘለአለማዊው እውነት አይደበዝዝም፣ አይቀነስም፣ ወይም አይጠፋም።

እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ እና የቤተክርስቲያኗን ሸንጎና ስራዎች በቅርብ እንደተመለከተ ሰው፣ ይህችን ቤተክርስቲያን ወይም አባላቷን በጥብቅ የሚነካ ምንም ነገር ውሳኔ መነሳሻ፣ መመሪያ፣ እና ድጋፍ በቅንነት ሳይፈለግበት የማይደረግ እንደሆነ በጥብቅ እመሰክራለሁ።  ይህች የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ናት። ቤተክርስቲያኑ ከተመደበላት መንገድ ያለ አላማ እንድትጓዝ ወይም መለኮታዊ እጣ ፈንታዋን ለማከናወን እንድትወድቅ እግዚአብሔር አይፈቅድም።

## ለእናንተም ክፍል አለ።

ከቤተክርስቲያኗ እራሳቸውን ለሚለያዩ ሁሉ፣ እንዲህ እላለሁ፣ ውድ ጓደኞቼ፣ በዚህ ለእናንተ ቦታ አለ።

ነ እናም ችሎታችሁን፣ ስጦታችሁን፣ እና ሀይላችሁን ጨምሩ። በዚህም ምክንያት የተሻልን እንሆናለን።

*አንዳንዶችም እንዲህ ይጠይቃሉ,“ግን ስለጥርጣሬዎቼስ?”*

ጥያቂ መኖር ከፍጥር የመጣ ነው— የታማኝ ጥያቄ ፍሬ በአብዛኛው ጊዜ ወደ ታላቅ መረጃ ዛፍ ያድጋልም ይጎለምሳልም። በአንድም ጊዜ ይሁን በሌላ፣ በጥብቅ ወይም ከስሜት በሚመጣ ጥያቄ የሚታገሉ ጥቂት የቤተክርስቲያኑ አባላት አሉ። ከቤተክርስቲያኗ አላማዎች አንዱ የእምነት ፍሬን መንከባከብ እና ማሳደግ ነው—ይህም የሚደረገው አንዳንዴ በጥርጣሬ አሸዋማ አፈር ውስጥ ነው። እምነት የሚታዩ ባይሆኑም እውነት በሆኑ ነገሮች ላይ ተስፋ የሚጣልበት ነው።[7]

ስለዚህ፣ ውድ ወንድሞቼና እህቶቼ—ውድ ጓደኞቼ— እባካችሁ፣ መጀመሪያ እምነታችሁን ከመጠራጠራችሁ በፊት ጥርጣሬያአችሁን ተጠራጠሩ።[8] ጥርጣሬ እንደ እስረኛ እንዳይዘን እና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚመጡት ከመለኮታዊ ፍቅር፣ ሰላም፣ እና ስጦታዎች እንዳናገኝ እንዳያደርገን በምንም መፍቀድ አይገባንም።

*አንዳንዱም እንዲህ ሊል ይችላል“በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ከእናንተ ጋር የምጣጣም አይመስለኝም።”*

ልባችን ውስጥ ለመመልከት ብትችሉ፣ ከምታስቡት በላይ ከእኛ ጋር አንድ እንደ ሆናችሁ ታገኛላችሁ። እኛ እንደ እናንተ አይነት ጉጉቶች እና ችግሮች እናም ተስፋዎች እንዳሉን በማወቅ ትደለቃላችሁ። የእናንተ የድሮ ህይወት ወይም አስተዳደግ የኋለኛውቀ ቅዱሳን ናቸው ብላችሁ ከምታስቡበት የተለየ ይመስላል፣ ነገር ግን ያም በረከት ሊሆን ይችላል። ወንድሞችና እህቶች፣ ውድ ጓደኞች፣ የእናንተን ልዩ ችሎታ እና አስተያየት ያስፈልጉናል። የሰው እና በአለም አቀፍ ያሉ ህዝቦች ልዩነት ከቤተክርስቲያኗ ጥንካሬ ነው።

*አንዳንዶች እንዲህ ይላሉ፣ “በእናንተ መሰረታዊ መርሆች ለመኖር የምችል አይመስለኝም።”*

ይህም ከሁሉም ይበልጥ ልትመጡበት የሚገባው ምክንያት ነው። ቤተክርስቲያኗ ፍጹም ያልሆኑትን፣ የሚታገሉትን፣ እና የደከሙትን ለመንከባከብ የተነደፈች ነች። ገና እነዚህን ያላሸነፏቸው ቢሆንም፣ በልባቸው በሙሉ ትእዛዛትን ለመጠበቅ ፍላጎትባላቸው ሰዎች የተሞላች ነች።

*አንዳንዶች እንዲህ ይላሉ፣ “ግብዝ የሆነ የቤተክርስቲያኗ አባልን አውቃለሁ። እንደ እርሱ አይነት አባል ካለው ቤተክርስቲያን ውስጥ አባል መቼም አልሆንም።”*

*ግብዝነትን* በሚያምንበት ወይም በምታ ምንበት ሁኔታ ፍጹም በሆነ ሁኔታ ለመኖር እንደወደቀ ትርጉም የምታስቡት ከሆነ፣ ሁላችንም ግብዞች ነን። ማንኛችንም እንደ ክርስቶስ አይነት መሆን እንዳለብን እንደምና ውቀው አይደለንም። ነገር ግን ስህተቶቻችንን እና ኃጢያት ለመስራት ያለን ጸባያችንን ለማሸነፍ የልብ ፍላጎት አለን። በልባችን እና በነፍሳችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ እርዳታ ጋር የተሻለ ለመሆን እንጥራለን።

እነዚህ የእናንተ ፍላጎቶች ከሆኑ፣ ጉዳዮቻ ችሁ፣ የግል ታሪካችሁ፣ ወይም የምስክራችሁ ጥንካሬ ምንም ቢሆኑ፣ ለእናንተ በዚህች ቤተክርስቲያን ክፍል አላችሁ። ኑ ከእኛ ጋር አንድ ሁኑ!

**ኑ ከእኛ ጋር ተቀላቀሉ!**

እንደ ሰው ፍጹም ባንሆንም፣ አለም ልታ ቀርባቸው ከምትችላቸው መልካም ነፍሳት ብዙዎቹን በዚህች ቤተክርስቲያን አባላት ውስጥ ለማግኘት እንደምትችሉ እርግጠኛ ነኝ። የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ደጉን እና የሚንከባከበውን፣ ታማኙን እና ትጉህ የሆነውን የምትስብ ይመስላል።

ፍጹም የሆኑ ሰዎችን ለማግኘት ከጠበቃ ችሁ፣ ትበሳጫላችሁ። ነገር ግን ንጹህ የክርስ ቶስ ትምህርትን፣ “የቆሰለ ነፍስን የሚፈውስ”[9] የእግዚአብሔርን ቃል እና የሚቀድስ የመንፈስ ቅዱስ ተፅዕኖን የምትፈልጉ ከሆነ፣ በዚህም እነዚህን ታገኛላችሁ። በዚህ በሚቀንሰው እምነት ዘመን— ብዙዎች ከሰማይ እቅፍ እየራቁ እንዳሉ በሚመስለው ዘመን— ልክ እንደ እናንተ እግዚአብሔርን እና ሰዎችን በማገልገል አዳኝን ለማወቅ እና ወደ እርሱ ለመቅረብ የሚጓጉ ሰዎችን ታገኛላችሁ። ኑ፣ ከእኛ ጋር ተቀላቀሉ!

**እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን?**

በአዳኝ ህይወት ውስጥ ብዙ ሰዎች ትተውት ስለሄዱበት ጊዜ አስታውሳለሁ።[10] ኢየሱስ አስራ ሁለት ሐዋሪያቱን እዲህ ብሎ ጠየቃቸው፥

“እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን?”

“ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፣ ጌታ ሆይ፥ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ።”[11]

እኛም እንደዚህ አይነት መልሶች ለዚህ አይነት ጥያቄ መመለስ ያለብን ጊዜዎች አሉ። እኛ ደግሞ ልንሄድ እንወዳለን? ወይም እንደ ጴጥሮስ የዘላለም ሕይወት ቃልን አጥብቀን እንይዛለን?

እውነትን፣ ትርጉምን፣ እና እምነትን ወደ ስራ የሚቀየርበት መንገድ ከፈለጋችሁ፤ የሚስማማችሁ ቦታ የምትፈልጉ ከሆናችሁ፥ ኑ፣ ከእኛ ጋር አንድ ሁኑ!

ያቀፋችሁን እምነት ትታችሁ የሄዳችሁ ከሆናችሁ፥ ተመለሱ። ከእኛ ጋር ተቀላቀሉ!

ተስፋ ለመቁረጥ ከተፈተናችሁ፥ ለጥቂት ጊዜ ቆዩ። እዚህ ለእናንተ ክፍል አለላችሁ።

እነዚህን ቃላት ለሚሰሙ እና ለሚያነቡ ሁሉ እንዲህ እለምናችኋለሁ፥ ኑ፣ ከእኛ ጋር አንድ ሁኑ! የደጉ ክርስቶስን ጥሪ አድምጡ። መስቀላችሁን አንሱ እና ተከተሉት።[12]

ኑ፣ ከእኛ ጋር አንድ ሁኑ! በዚህም ዋጋ ካለው በላይ ምን ውድ እንደሆነ ታገኛለችሁ።

የዘለአለም ቃልን፣ የተባረከ ቤዛነት ቃል ኪዳንን፣ እና የሰላምና የደስታ መንገድን እንደምታገኙ እመሰክራለሁ።

ለእውነት የምትፈልጉበት በልባችሁ ውስጥ መጥታችሁ ከእኛ ጋር አንድ እንድትሆኑ ፍላጎት እንዲሰጣችሁ እጸልያለሁ። በቅዱሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ አሜን።

**ማስታወሻዎች**

1.1. ማቴዎስ 16፥18–19፣ ሒላማን 10፥7 ተመልከቱ።
2.2. ትምህርት እና ቃል ኪዳን 84፥20 ተመልከቱ።
3. 2 ኔፊ 33፥10 ተመልከቱ።
4. “Have I Done Any Good?” ተመልከቱ *Hymns*, no. 223።
5. የእምነት አንቀፅ 1፥11 ተመልከቱ
6. የመፅሐፈ ሞርሞን መግቢያ ገጽ፤ ሞርሞን 8፥7 ተመልከቱ።
7. ዕብራውያን 11፥1፣ አልማ 32፥21 ተመልከቱ።
8. ኤፍ. ኤፍ. ቦስዎርዝ፣ *Christ the Healer* (1924)፣ 23 ተመልከቱ።
9. ያዕቆብ 2፥8።
10. ዮሀንስ 6፥66 ተመልከቱ።
11. ዮሀንስ 6፥67–68።
12. ማቴዎስ 16፥24።

© 2013 by Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/13 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/13 (እ.አ.አ) *Visiting Teaching Message, November 2013*. Amharic. 10671 506 ትርጉም